# ማዕዶት



ከግንቦት ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም ጀምሮ የካቴድራል ነት ማዕርግ የተሰጠው የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ይህ ነው ። (አ.አ.)

መስከረም ፲፱፻፹፬ ዓ/ም
ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማዕዶት

መስከረም ፲፱፻፹፬ ዓ/ም
አዲስ አበባ

ቍጥር ፴፭

www.ethiopianorthodox.org

እባክህ ንገረን አንተ ቄስ አንተ ሰው ፤

ንስሐ እርሳስ ላጺስ የትነው የሚ ሸጠው ብለን ብንጠይቀው ፤
እኔ የገዛሁት ከዮሐንስ ሱቅ ነው ፤
አትርፋችሁ ግዙኝ እኔም ልሸጠው ነው ፤

ብሩ መለሰልን ምን ዓይነት ካህን ነው ፤

ሌላ እማራጭ የለም እኛም ልንገ ዛው ነው ፤

ወረቀት ልባችን ድልዙ ብዙ ነው ፤
ጥርት የሚያደርገው ንስሐ ላጺስ ነው ፤

(አምላክ) መምህሩ ሳይመጣ ደብ ተሩን ሳይወስደው ፤

ቶሎ ብለን ገዝተን አሁኑን ማጽ ዳት ነው ፡፡
አምላክ ፊት ለመቅረብ በጣሙን ችግር ነው ፤
እንደገሠገሡ መግቢቱ ጭንቅ ነው ፤
በታች በር በላይ በር ኃይለኛ ዘብ አለው ፤
ንስሐን ጠይቋት ዘወ ንስሐ ነው ፤
እሱ ከፈቀደ መግቢቱ ቀላል ነው ፤
ንስሐ ዮሐንስ የጸፃታው ጅም ነው
ንስሐ ሳወቀው ለካስ ጠቃሚ ነው ፤
ይህን የጠቆመን ዮሐንስ መጥምቅ ነው ፤
ድሮም መንገድ መምራት ለሱ ተሰ ጥዎ ነው ፤
ኃጢአትና በደል ሰውን ያኝካሉ ፤
በነኃ በጠባ እዳምን ያግሉ ፤

በጣም ተናደዋል ያዳም ልጆች እሉ ፤እንዴት ልጅ እለችው የምት በልጥ ክሁሉ ፤

ኃይለኛ ልጅ ያላት የሚያድን በቃሉ ስሟም ማርያም ነው ወላዲተ ሆሉ፤
ኃጢአትና በደል አለን አለን ሲሉ ፤
በኃይለኛ ልጅዋ ተደመሰሱ እሉ ፤
ካዳም ላይ ከንገዲህ ጭራሽ ይፋ ቃሉ ፤

ከጭንቅ ለመዳን ጭንቅ ያለን በ ሙሉ ፤

እስኪ ባጠቃላይ ማርያም ማርያም በሉ ፡፡

አዘጋጁ ከአላባ ቁሊቶ ከተማ ንግድ ባንክ መልእኩ አከለ ቤተ ውልኝ ፖ ሣ ቁ ፩



www.ethiopianorthodox.org